# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 145 የካቲት 17 2003 ገጽ 1


**በአፍሪቃ ምድር በየእለቱ ታሪክ እየተሰራ ነው!!!**

**የጋዳፊ የስልጣን ክር ቀጥና ልትበጠስ በደረሰችበት በአሁኑ ሰዓትም በቴሌቪዥን ባደረገው ንግግር ህዝብ በእሱ ጋር እንደሆነ፤ ሁሉም ነገር በቁጥጥሩ ሥር እንዳለ ቀባጥሯል፤ ተቃዋሚዎቹንም ዘልፏል። መለስ ዜናዊ ባለፉት ሃያ ዓመታት የኖረበት ሁኔታ የዚሁ ተመሳሳይ ነው። መለስም መውደቁ አይቀርም። የመለስ ውድቀት ከጋዳፊ ውድቀት የባሰ ይሆናል።**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ወያኔ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከፍተኛ ወታደራዊ ሥምሪት እያደረገ ነው

በቱኒዚያ የፈነዳውና ከሰሜን አፍሪካ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ የተዛመተው ህዝባዊ አብዮት ያስደነገጠው ዘረኛው መለስ ዜናዊና ፋሽስት ግብረ አበሮቹ በአዲስ አበባ ታላላቅ መንገዶችና ጉራንጉር ሠፈሮች ሳይቀር ከፍተኛ ቁጥር ያለውን የደህንነት፤ የፖሊስና የመከላከያ ሰራዊት ሃይል ማሰማራታቸውን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ በላከው ሪፖርት አስታውቆአል።

የብሄር ብሄረሰቦች መብት ለመጀመሪያ ጊዜ በአገሪቱ እንዲከበር በማድረጌና ልማት እና እድገት በማምጣቴ ህዝብ 99.6 % በሆነ ድምጽ  መርጦኛል የሚለው ወያኔ አገኘሁ ያለውን የህዝብ ድጋፍ ለግማሽ አመት እንኳን በወጉ ሳያጣጥም ሊነሳብኝ ይችላል ብሎ ስጋት ውስጥ የከተተውን ህዝባዊ አመጽ በሃይል ለመደፍጠጥ፣ የመናገሻ ከተማውን ትላልቅና ትናንሽ መንገዶች በሙሉ የጦር ሜዳ ይመስል በወታደር ሃይል አሳጥሮታል እንደዘጋቢያችን ሪፖርት።

በድህረ ምርጫ 97 የተነሳውን ህዝባዊ ተቃውሞ በጠመንጃ ሃይል የሚበትን አጋዚ የሚባል ቅልብ ሠራዊት በአዲሳ አበባ ዋና ዋና መንገዶች ላይ በማሰማራት ከ200 በላይ ንጹሃን ዜጎችን ያስጨፈጨፈው ወያኔ የአያሏን አገር አመሪካ ድጋፍ በማግኘት የሰራውን ወንጀል ለማድበስበስ ሲል ወደ ጎሬቤት ሱማሌ ገብቶ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ሱማሌ ዘጎችን በገዛ አገራቸው አንደጨፈጨፈ ሂውማን ራይትስ ዎች የተባለው ታዋቂው የሰብ አዊ መብት ተከራካሪ ድርጅት አጋልጦ ነበር። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በጋምቤላ ክልል ከ4000 ሄክታር በላይ ጥብቅ ተፈጥሮ ደን ተጨፈጨፈ

በጋምቤላ ክልል በአይነቱ ልዩ የነበረና ለዘመናት ተከብሮና ተጠብቆ የኖረ በመዠንገር ዞን ጎደሬ ወረዳ ጉማሬ ቀበሌ የሚገኝ ከ4000 ሄክታር በላይ ጥብቅ የተፈጥሮ ደን እየተመነጠረ መሆኑን ዘጋቢያችን በቦታው የነበሩ አይን እማኞችን በመጥቀስ ከላከልን ዘገባ ለማወቅ ተችሎአል።

እንደ ዘጋቢያችን ሪፖርት ይህን ያህል ስፋት ያለውንና ለዘመናት ተጠብቆ የኖረ ደን እየጨፈጨፈ የሚገኘው ለእርሻ ልማት በሚል ሽፋን ዘረኛው አምባገነን አገዛዝ በሽያጭ ያስረከበው Vendata Harvests PLC. የተባለ የህንድ ኩባንያ እንደሆነ ታውቁአል ለቬንዳታ ኩባንያ የተሰጠዉ በተፈጥሮ ደን የተሸፈነዉ 4000 ሄክታር የሚሆን ለም መሬት የአካባቢዉን ኗሪዎችና እጂግ ማስቆጣቱንና አንዳንድ የአካባቢ ተፈጥሮ ተቆርቋሪዎችን እያነጋገረ መሆኑም ተያይዞ የደረሰን ዝገባ አሳይቱአል::

በተጠቀሰዉ ስፍራ የደን ጭፍጨፋውን እያካሄደ የሚገኘው የህንድ ኩባንያ የተፈጥሮ ደኑን መንጥሮ የሻይ ተክል ለመትከል መዘጋጀቱ የተገለጸ ሲሆን አንዳንድ  ባለሙያዎች በተፈጥሮ ደኑ ላይ ሊከተል የሚችለውን ጭፍጨፋ በመገመት ቢያንስ ባለሃብት ተብየው ከሻይ ተክል የልቅ  የቡና ተክል ቢተክል ቢያንስ ለጥላ ሲባል ከፊሉ የደን አካል ሊተርፍ ይችል እንደነበር ቢናገሩም ሰሚ አጥተው እንደቀሩ ታውቁአል ዘጋቢያችን ያናገራቸው አንድ የጎደሬ ወረዳ የግብርና ልማት ሰራተኛ የኢትዮጵያ የደን ሽፋን ከሶስት በመቶ እንደሆነ እየታውቀ እንዲህ አይነት ውድመት መፈጸሙ ዘረኛው የወያኔ አምባገነን አገዛዝ ሃገር የማጥፋት ተልእኮዉን በተግባር እያሳየ ለመሆኑ መረጃ ነው ብለዋል።

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በዋሺንግተን የወንድማማቾች ቀን በሚል ስያሜ የሚጠራ ከፍተኛ ሰላማዊ ሰልፍ ሊካሄድ መሆኑ ታወቀ

ማርች ፎር ፍሪደም በመባል የሚታወቀውና በውጭ ሃገራት የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንን በማስተባበር ላይ የሚገኘው ኮሚቴ በቅርቡ በዋሽንግተን ዲሲ ዋይት ሃውስ ፊት ለፊት  የወንድማማቾች ቀን በሚል ስያሜ የሚጠራ ከፍተኛ ሰላማዊ ሰልፍ ሊያካሄድ መሆኑን ባወጣው መግለጫ ላይ አስታውቁአል ማርች ፎር ፍሪደም ባወጣው በዚሁ መግለጫው  ዛሬ በዓለማችን ዙሪያ ለነፃነት፣ ለእኩልነት፣ ለሰብአዊ መብትና ለዲሞክሲ ስርዓት መከበር ህዝቦች እጅ ለእጅ ተያይዞው፣ መድፍና ታንክ ሳይበግራቸው እምቢ ለነፃነቴ፣ እምቢ ለመብቴ፣ እምቢ ለሰብአዊ ክብሬ ብለው አደባባይ በመውጣት ለዘመናት ሲጨቁኑዋቸው የነበሩ አምባገነናዊ ስርዓቶች በህዝባዊ ዓመፅና በተባበረ ክንድ ከዙፋናቸው በሀይል መንግለው ሲጥሉዋቸው በዓይናችን እያየን ነው ብሉአል።

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## በአዲስ አበባ ሳሪስ ሁለት ወጣቶች ተገድለውና ተጥለው ተገኙ

ዘረኛውና ግፈኛው የወያኔ አገዛዝ በቱኒዚያ ተቀጣጥሎና የሰሜን አፍሪቃ ሃገራትን አዳርሶ ወደምስራቁ ክፍል እየገሰገሰ ያለው ህዝባዊ ማእበል በፈጠረበት ጭንቀት ምክንያት የሚያደርገው ተግባር ሁሉ የ እብድ ስራ እየሆነ መምጣቱን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ በላከልን ሪፖርትት ገለጸ እንደ ዘጋቢያችን ሪፖርት በአዲስ አበባ ከተማ ሳሪስ ተብሎ በሚጠራው  አካባቢ ሁለት ወጣቶች በአሰቃቂ ሁኔታ ተገድለውና አንደኛው ወጣት አይኖቹ እንዲወጡ ተደርጎ ድልድይ ስር ተጥለው መገኘታቸውን ተገልጾአል።  ወጣቶቹ ከመሞታቸው በፊት በቱኒዚያና በግብጽ ስለነበረው ህዝባዊ አመጽ በስፋት ይከታተሉ የነበሩ እንደሆኑ የተገለጸ ሲሆን ግድያውን የፈጸመው የወያኔው ዘረኛ አገዛዝ ለመሆኑ ምንም ጥርጥር እንደሌላቸው አንድ ስማቸው እንድይገለጽ የፈለጉ የሳሪስ ነዋሪ ገልጸዋል።

ዘጋቢያችን የሙዋቾችን ትክክለኛ ማንነት ለማወቅ እየጣራ የሚገኝ ሲሆን በአካባቢው ከነበሩ አንዳንድ ግለሰቦች ባገኘው መረጃ መሰረት፣ ወጣቶቹ ከየቤቶቻቸው በታጣቂዎች ምሽት ላይ ተወስደው እንደነበርና፣ በጃቸው ይዘውት የነበረ የሞባይል ስልኮችና መታወቂያዎቻቸውም የተወሰዱ መሆኑ ታውቁአል::

በሌላ በኩል በተያያዘ ዜና በሰሜን አፍሪቃ ህዝባዊ አብዮት ከተቀጣጠለ ወዲህ እንቅልፍ አጥተው ያሉት የዘረኛው አምባገነን አገዛዝ ቡድን አባላት የሚይዙና የሚጨብጡትን እያጡ ከመምጣታቸው በተጨማሪ፣ ኢትዮጵያዊያን ነጻ ከሆኑ የዜና አውታሮች መረጃዎችን እንዳያገኙ በተለያየ መንገድ መሰናክል እየፈጠሩ እንደሚገኙ ታውቁአል  ከዚሁ ጋር ተያይዤ ኢትዮጵያ ውስጥ አልጃዚራ የቴሌቪዥን ፕሮግራም በዘረኛው የወያኔ አገዛዝ መታፈኑም ተሰምቱአል። አልጃዚራ የዜና አውታር የሰሜን አፍሪቃ ሃገራቱን አብዮት በስፋትና በቀጥታ በመዘገብ የዓለም ህዝብ በየሃገራቱ እየተካሄዱ ያሉ ኩነቶችን እንዲያውቅ ና እንዲከታተል ሲያደርግ መቆየቱ ይታወሳል።(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## አዲስ አበባ ከተማ ፊንፊኔ ተብላ እንድትጠራ ዘረኛው የወያኔ ስርአት አዲስ ዘመቻ እንደጀመረ ታወቀ

ኢትዮጵያዊያንን በዘር፣ በሃይማኖት፣ በጎሳና በተለያዩ መንገዶች በመከፋፈልና በማናቆር እድሜውን እያራዘመ የሚገኘው ዘረኛው የወያኔ አምባገነን አገዛዝ የአዲስ አበባ ከተማ ፊንፊኔ ተብላ እንድትጠራ ውስጥ ለውስጥ እንቅስቃሴ መጀመሩን ለአገዛዙ ባለስልጣናት ቅርበት ያላቸው ምንጮቻችን ገለጹ እንደውስጥ ምንጮቻችን ዘገባ በተለይም በቅርብ ቀን የኦነግ ፤ የግንቦት7 እና የትግራይ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ አመራር አባላት ለኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን በጋራ በሰጡት ቃለመጠይቅ የዲሞክራሲና የህዝቦች አንድነት እንቅፋት የሆነውን ዘረኛ የወያኔ አገዛዝ በጋራ ለመፋለም ከምንጊዜውም በላይ  ተቀራርበው እየተነጋገሩ መሆናቸውን ከገለጹ ቦኋላ በተቃዋሚ ፓርቲዎቹ የአላማ አንድነት ተደናግጦ እንደሆነና በዚህ አዲስ እርምጃ ህዝብ ይከፋፈልልኛል ከሚል ከንቱ ተስፋ እንደሆን ለማወቅ ተችሎአል።

ይህን አዲስ የወያኔ ጥረት አስመልክቶ አስተያየታቸውን እንዲሰጡን የጠየቅናቸው በአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ  የሆኑ የኦሮሞ ብሄረሰብ ተወላጅ በሰጡን አስተያየት፣ የወያኔው ዘረኛ አገዛዝ ከምርጫ 97 በፊት  የኦሮሚያ ክልል ጽ|ቤት በሃይል ወደ አዳማ እንዲዛወር ካደረገና ውሳነውን የተቃወሙትን የኦሮሞ ተወላጆች ከኦሮሞ ነፃነት ግንባር ጋር በመፈረጅ ከፊሉን ከመንግሥት ሥራ በማባረር ፤ በማሠር እና በመግደል ውሳኔው ተግባራዊ እንዲደረግ ከተደረገ እና በርካታ መሥሪያቤቶች ወደ ክልሉ ተጉዘው መሥሪያቤቶቻቸውን ካሳነጹ ቦኋላ በምርጫ 97 በደረሰበት ሽንፈት ነፍጠኞች ዋና ከተማውን መልሰው ሊቆጣጠሩ ነውና በአስሸኳይ ተመለሱ ብሎ በማዘዙ ብዙዎች  በገነቡት ህንፃ ለአመት እንኳ ሳይሰሩ እንደተመለሱ አስታውሰው የአሁኑም ውሳኔ እንደያኔው የህዝቡን ተቃውሞ ለመከፋፈልና ደጋፊ በማፍራት የሥልጣን እድሜ ለማራዘም የታቀደ ወያኔያዊ ዘዴ ከመሆን ውጪ ሊሆን አይችልም ብለዋል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የአዲስ አበባ ቤት አከራዮች 40 በመቶ ታክስ ክፈሉ አለ

በአዲስ አበባ ከተማ የሚኖሩና የቤታቸውን ክፍል በማከራየት ኑሮአቸውን በመደጎም የሚተዳደሩ ነዋሪዎች ከሚያገኙት ገቢ አርባ በመቶ ለአገዛዙ ገቢ እንዲያደርጉ መጠየቃቸውን የግንቦት ሰባት ዘጋቢ ከአዲስ አበባ ባስተላለፈው ዘገባ ገለጸ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ በተለይም አዲስ አበባን ጨምሮ የሚገኙ ታላላቅ ከተማ ነዋሪዎች ሊቋዋቋዋሙት እያስቸገራቸው ያለውን የኑሮ ውድነት ለመጋፈጥ ከሚጠቀሙት ዘዴ አንደኛው ያለቻቸውን አነስተኛም ቤት ቢሆን እየከፈሉ፣ በማከራየት መጠነኛ ገቢ ማግኘት መሆኑ ይታውቃል።

ዘጋቢያችን ያነጋገራቸውና ቀደም ብሎ ከነበረቻቸው ሁለት ክፍል ቤት በአንደኛው እየኖሩ  ሌላኛውን ክፍል በወር አራት መቶ ብር እያስከፈሉ የሚኖሩ ወይዘሮ እንደተናገሩት፣ ኑሮአቸውን እየገፉ ያሉት (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ጋዳፊ - መለስ፤ መለስ - ጋዳፊ

በአፍሪቃ ምድር በየእለቱ ታሪክ እየተሰራ ነው!!!

የሊቢያ ብቻ ሳይሆን የመላው አፍሪካ ንጉሠ ነገሥት ነኝ ባዩ "አፄ በጉልበቱ" የኮሎኔል ሙአመር ጋዳፊም ወንበር ተነቃንቋል። ጋዳፊ ለአርባ ሁለት ተከታታይ አመታት ሊቢያን ገዝቷል፤ በሊቢያ ሃብት ተንደላቋል፤ የመጣለትን እየተናገረ፤ ያሻውን እየፈፀመ ተጨማልቋል። እንኳንስ በሃገሩ በአፍሪካ ኅብረትም "ሃይ" የሚለው አጥቶ ተሞላቋል።

አሁን ግን እየመሸበት ነው። ሊቢያዊያን ደፍረው አምባገነንነቱ ነግረውታል። "ልቀቅ፣ ውጣ፣ አንፈልግህም" ብለውታል። እንደ ቅዱስ ቁርዓን ሊታይ ትንሽ ቀርቶት የነበረው አረንጓዴ መጽሃፉ በአደባባይ ተቃጥሏል። በአረንጓዴ አደባባይም "ጋዳፊ ውረድ!!!" ተብሎ ተጮሆበታል። ከእንግዲህ ሊቢያ የቀድሞዋ ሊቢያ እንደማትሆን በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል።

ጋዳፊ በግብዝነትና ጭካኔ መለስን የሚመስል አምባገነን ነው። መለስ ገና ሚኒሊክ ቤተመንግስት ከመግባቱ በፊት ጀምሮ የጋዳፊ ወዳጅና አድናቂ እንደነበረ ይታወቃል። ራሱ ጋዳፊ ከመለስ ጋር ስለነበራቸው ወዳጅነት ብቻ ሳይሆን ከዚያም ያለፉ የመለስ ሴራዎችና ተንኮሎችን በግዴለሽነቱ ይፋ አድርጓቸዋል። መለስና ጋዳፊ ተመሳሳይ እኩይ ባህሪያት ናቸው።

ዛሬ ጋዳፊ በራሱ ህዝብ ላይ እየፈጸማቸው ያሉ ተግባራት መለስ ዜናዊ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ፈጽሟቸዋል። ለአብነት ያህልም የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል።

1. ጋዳፊ በቀን አምስት መቶ ዶላር የሚከፈላቸው ቅጥር ነብሰ ገዳዮችን ከጎረቤት አገራት እያስመጣ በራሱ ህዝብ ላይ አሰማርቷል። እነዚህ ቅጥር ነፍሰ ገዳዮች ህፃን፣ አዋቂ፤ ወንድ፣ ሴት ብለው ሳይመርጡ ሊቢያዊያንን በጠራራ ፀሃይ ጨፍጭፈዋል። መለስ ዜናዌም በተለያዩ ጊዜዓት ተመሳሳይ ተግባር በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ፈጽሟል። በተለይም በምርጫ 97 ማግሥት የሰለጡኑ ነብሰ ገዳዮችን በማሰማራት ህፃንና አዋቂን፤ ወንድና ሴትን ሳይለዩ በጭፍን ጨፍጭፈዋል። ልዩነቱ መለስ ነብሰ ገዳዮችን ከሌላ አገር ማስመጣት ሳያስፈልገው ከአገር ውስጥ መመልመል መቻሉ ብቻ ነው።
2. ጋዳፊ የራሱን ህዝብ በጦር ሠራዊት አስደብድቧል። አልታዘዝ አሉት እንጂ ሰላማዊ ሰልፈኖችን በአይሮፕላን ለማስደብደብ ትዕዛዝ ሰጥቶ ነበር። መለስ ዜናዊም በጦር ሠራዊት ህዝብን አስደብድቧል። በአይሮፕላንና ታንክ ሳይቀር ሰላማዊ ህዝብና መንደሮችን አውድሟል። ኦጋዴን፣ ጋምቤላና አዲስ አበባ ቋሚ ምስክሮች ናቸው። በዚህ ረገድ በጋዳፊና በመለስ መካከል ያለው ልዩነት ጋዳፊ ከልቡ "ህዝቤ" በሚለው ላይ የዘመተ ሲሆን መለስ ግን ከልቡ "ህዝቤ" የሚለው የሌለ መሆኑ ነው።
3. ጋዳፊ ህዝብን በህዝብ ላይ አነሳስቶ ሊቢያውያን እርስ በእርስ እንዲጨፋጨፉ ሁኔታዎችን እያመቻቸ ነው። ደጋፊዎቹን " አይጦችን አደባባይ ወጥታችሁ ግጠሟቸው" ሲል ይፋ ጥሪ አድርጓል። በዚህ ነጥብ መለስ ጋዳፊን በብዙ እጥፍ ይበልጠዋል። ጋዳፊ ይህንን ተግባር የፈፀመው በያዝነው ሳምንት ሲሆን መለስ ግን ይህንኑ ተግባር ባለፉት ሃያ ዓመታት በተከታታይ ሲፈጽመው የነበረ ጉዳይ ነው።
4. ጋዳፊ የነፃነት ታጋዮችን "ወሮበሎች"፣ "ከሃዲዎች"፣ "አይጦች" እያለ ሰድቧቸዋል፤ አዋርዷቸዋል። መለስ የነፃነት ታጋዮችን "ከሃዲዎች"፣ "ፀረ-ሰላም ኃይሎች"፣ ፀረ-ልማት ኃይሎች"፣ "አደገኛ ቦዘኔዎች"፣ "ነፍጠኞች" እያለ ሰድቧቸዋል፤ አዋርዷቸዋል።
5. ጋዳፊ ተቃውሞ ሲጠነክርበት ህዝብ መረጃ እንዳያገኝ አልጀዚራን አፈነ፤ ኢንተርኔትና ቴሌፎንን አወከ። መለስ ዜናዊ እንዲህ ዓይነቱን ሥራ በደነገጠ ቁጥር የሚያደርገው ነገር ነው። ጋዜጠኞችን ማዋከብ፤ የራድዮና የቴሌቪዥን ሞገዶችን ማወክ የተለመደ ተግባሩ ነው። አሁንም የኢትዮጵያ ህዝብ የባልደረቦቹን ውድቀት እንዳይመለከት አልጀዚራን አፍኗል።

የጋዳፊ የስልጣን ክር ቀጥና ልትበጠስ በደረሰችበት በአሁኑ ሰዓትም በቴሌቪዥን ባደረገው ንግግር ህዝብ በእሱ ጋር እንደሆነ፤ ሁሉም ነገር በቁጥጥሩ ሥር እንዳለ ቀባጥሯል፤ ተቃዋሚዎቹንም ዘልፏል። መለስ ዜናዊ ባለፉት ሃያ ዓመታት የኖረበት ሁኔታ የዚሁ ተመሳሳይ ነው። መለስ ከሃቅ ጋር አይተዋወቅም፤ የህዝብ ልብ የት እንዳለ አያውቅም፤ ትዕቢተኛ ነው፤ ሰዎችን መዝለፍ ብልህነት ይመስለዋል።

በቴሌቪዥ መስኮት ላይ ጠረጴዛ እየደበደበ ጮሆ በመናገር ጠንካራ መስሎ ለመታየት ቢሞክርም ጋዳፊ መውደቁ አይቀርም። ምናልባትም ይህ ርዕሰ አንቀስ ሳይታተም ሊወድቅ ይችል ይሆናል። አሊያም ጥቂት ቆይቶ ይወድቃል። የጋዳፊ አወዳደቅ ከቱኒዚያው ቤን ዓሊ እና ከግብጹ ሆስኒ ሙባረክ አወዳደቅ የከፋ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም። ከአሁኑ በሰብዓዊነት ላይ በሚደረግ ወንጀል እና በዘር ማጥፋት ወንጀል እንዲከሰስ አቤቱታዎች ከያቅጣጫው እየተሰሙ ነው። መለስም መውደቁ አይቀርም። ጋዳፊ በሳምንት ጊዜ ውስጥ የሠራውን መለስ በአስርት ዓመታት ጊዜ ሠርቷልና የመለስ ውድቀት ከጋዳፊ ውድቀት የባሰ ይሆናል።

የጋዳፊን ውድቀት ለማየት ብዙ መጠበቅ እንደማያስፈልገን ሁሉ የመለስን አስከፊ ውድቀት ለማየት ብዙ መጠበቅ አያስፈልገን ይሆናል። እርግጥ ነው እንዲህ ዓይነቶቹን ነቀርሳዎች ለመገላገል ዋጋ መክፈል የማይቀር እዳ ነው።

• • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • • •

## ዘረኛው መለስ ዜናዊ ኢሳት ከአየር ላይ የሚወርድበት ዕቅድ ተነድፎ እንዲቀርብለትአስቸኳይ መመሪያ አስተላለፈ

ላልፉት 20 አመታት በስታሊናዊ ጥብቅ የደህንነትና ወታደራዊ ሃይል ኢትዮጵያ አገራችንና ህዝቦቿን በጉልበት አፍኖ እየገዛ ያለው የመለስ ዜናዊና ጥቂት ግብረ አበሮቹ ቡድን ኢሳት የተባለው ነጻ የሚዲያ ተቋም የሚያስተላልፈው መረጃ ለሥልጣን ዕድሜው ስላሰጋው በአስቸኳይ የሚታፈንበት መንግድ ተጠንቶ እንዲቀርብለት ለጀሌዎቹ ሰሞኑን ት ዕዛዝ ማስተላለፉን የግንቦት 7 መረጃ ምንጭ አስታወቀ።

እንደግንቦት 7 መረጃ ምንጭ መለስ ዜናዊ ይህንን ትዕዛዝ ያስተላለፈው የህወሃት አባል እና የአገሪቱ ኢንፎርሜሽን ቴክኒ ኦሎጂ ሚንስቴር በሆነው ገብረጽዮን ገብረሚካኤል ሰብሳቢነት ለሚመራው ፤ ከኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒከሽን ፤ ከሳይንስና ቴኪኒ ኦሎጂ፤ ከወታደራዊ ኢንጂኔሪንግ፤ ከመብራት ሃይል፤ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲት ኤሌክትሪካል ኢንጂነሪንግ ዲፓርትመንት እና ለዚሁ ሥራ ተብሎ ከቻይና አገር ለመጡ የኤክስፐረቶች ቡድን ነው። ዜረኛውና ፋሺስቱ መለስ ዜናዊ መመሪያ አዘል ትዕዛዙን በሰጠበት ወቅት " እጅግ የሰለጠነ ዘመናዊ መሣሪያ ከታጠቀ 10 ብርጌድ በላይ መንግሥታችንን ለማናጋት አቅም ያለውን ይህንን በምራባዊያን የተከፈተብንን የፕሮፖጋንዳ ዘመቻ ቴለቪዝን በምንም መነገድ ተሸክመን መኖር የለብንም ስለዚህም ገንዘብ ሊገዛው የሚችል ማንኛውም የቴኪኒ ኦሎጂ ዕውቀት፤ መሳሪያና የሰው ሃይል ተመድቦ ከሳምንት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ፡ከአየር እንዲወርድ መድረግ አለበት ፤ ለዚህ የሚያስፈልገውን ማንኛውንም ወጪ አጥንታችሁ ከአንድ ሳምንት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለኔ በቀጥታ ልታቀርቡልኝ ይገባል " ማለቱ ታውቆአል።

ወያኔ ቀደም ሲል ኢሳትን ለማጥፋት አረብሳት በተባለው ካምፓኒ ባለሥልጣናት ላይ ከፍተኛ የሆነ ዲፕሎማቲክ ጫና ከመፍጠር አልፎ ከፍተኛ መጠን ያለው የአገሪቱን ሃብት በማፍሰስ ከቻይና የሳታላይት መጥለፊያ መሳሪያ አስገብቶ በሴሜን ተራራማ ቦታዎች ላይ እንደተከለ ከአረብ ሳት የተገኘው መረጃ እንደሚያረጋግጥ ኢሳት አስታውቆ እንደነበር አይዘነጋም ። ኢሳት ከአረብ ሳት ላይ ከወረደ ቦኋላ በታይኮምሳት በኩል የሚያስተላልፈው ስርጭት ተመሳሳይ በሆነ የወያኔ ጣልቃ ገብነት ለ24 ሰ ዓት ያህል ተቋርጦ እንደነበረና ወዲያውኑ የሳታላይት ካምፓኒ በመቀየር ወደ አየር እንደተመለሰ ይታወቃል። አድማጮቻችን የኢሳት ማኔጅመንት ቦርድ በዚህ መረጃ ላይ የሚሰጠውን አስተያየት ካለ በሚቀጥለው ፕሮግራማችን ይዘን ለመቅረብ እንደምንሞክር እንገልጻለን።

## ዘረኛው የወያኔ አምባገነን አገዛዝ የሃይማኖት ተቋአማትን የማዋርደ ስራውን ቀጥሉአል

ከሁለት ቀናት በፊት በአዋሳ ገብሬል ቤተክርስቲያን በተነሳ ግጭት ቁጥራቸው በውል ያልታወቀ ምእመናን መቁሰላቸውን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ዘገበ እንደ ኢሳት ዘገባ ከሁለት ቀናት በፊት በምእመናን መካከል በተነሳ አለመግባባት በተፈጠረ ግጭት የቆሰሉ ሰዎች ወደሆስፒታል መወሰዳቸውን የተገለጸ ሲሆን ፣ የቅዱስ ገብሬል ቤተክርስትያንም ከትናንት በስቲያ ጀምሮ በፖሊስ ቁጥጥር ስር መዋሉንና ምእመናኑም ወደ ቤተክርስቲያኑ እንዳይገቡ ተከልክለዋል፣ ውጥረቱ አሁን ድረስ እንዳለ ነው ብሉአል።

ኢሳት ከዚሁ ጋር አያይዞ እንደዘገበው የዘረኛው የወያኔ አምባገነን አገዛዝ ባለስልጣናትና ለፍርፋሪ ጥቅም ሲሉ ለወያኔ በማደር እራሳቸውንና ወገናቸውን በማዋረድ ተግባር ላይ የተሰማሩ ሆድ አደሮች በሃይማኖት ሽፋን የፖለቲካ ቅስቀሳ እያካሄዱ እንደሆነ አጋልጦአል። ወያኔ ሃይማኖታዊ ስብከት የሚሰብኩ ሰዎች ከመንግስት ፈቃድ እንዲወስዱ የሚያደርግ መመሪያ እየወጣ እንደሆነም አያይዞ ዘግቦአል።

ኢትዮጵያ ውስጥ ከሃይማኖት ጋር በተያያዘ የሚነሱ ግጭቶች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየጎሎ መጥተዋል፣ያለው ኢ ሳት ቀደም ብሎ የዘረኛው አምባገነን አገዛዝ ባለስልጣን ተፈራ ዋልዋ በምርጫ 97 ወቅት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የነፍጠኛው መሸሸጊያ ዋሻ ናት ማለቱን ፣ ኢህአዴግ የሙስሊሙ ህብረተሰብ አጋዥ ነው በማለትም ይቀሰቅስ እንደነበር አስታውሱአል።

የሃይማኖት ግጭቶች የድህነቱ የርሃቡና የሙብት አፈናው መገለጫዎች መሆናቸውን ምሁራን ይናገራሉ ያለው ኢሳት ፣ አገዛዙ በሃይማኖት ሃይማኖትም በመንግስት ጉዳይ ጣልቃ እንደማይገቡ የይስሙላው ህገ መንግስት ቢደነገግም በስልጣን ላይ ያሉት የአምባገነኑ አገዛዝ ቁንጮዎች የሃይማኖት አባት ተብየዎችን እንደፈለጉት እንደሚያሽከረክሩአቸው ምእመናን ይናገራሉ ብሎአል።

የመለስ አምባገነን አገዛዝ በተለያዩ ጊዚያቶች ከኢትዮጵያ ህዝብ እየገጠመው ያለውን ፈተና ለመቋቋም የተለያዩ ስልቶች ሲጠቀም እንደቆየና ህዝብ እርስ በርሱ እንዳይተማመን ለማድረግ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሃይማኖት ዙሪያ መከፋፈልና ግጭት እንዲፈጠርም ሌት ከቀን እየሰራ እንደሆነ በተደጋጋሚ ስንዘግብ መቆየታችን አይዘነጋም።

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታሳጥን ቁጥር ፡- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

# የሰሜን አፍሪቃ ህዝባዊ አመፆችና ያገራችን እጣ ፈንታ

ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ እሁድ ፌብሩዋሪ 13፣ 2011 ዓ:ም. በዳላስ ከተማ ግንቦት ሰባት በጠራው ህዝባዊ ስብሰባ ላይ የቀረበ ንግግር: ክፍል 1

ሆሳም ካሊፍ የ50 አመት እድሜ ባለጸጋ የሆነ ግብጻዊ መሃንዲስ ነው:: ጣህሪር አደባባይ ሲዘዋወር ያገኘውን አንድ ምእራባዊ ጋዜጠኛ ተጠግቶ እኛ ከቱኒዝያ ምን እንደተማርን ታውቃለህ? ይለዋል:: የደረሰን መልእክት የሚለው "ራስህን አታቃጥል: ማቃጠል ያለብህ በውስጥህ የሰፈረውን ፍርሃት ነው:: የሚለውን መልእክት ነው" ይለዋል::

የዚህን የጣህሪር አደባባይ ትእይንት የሚመለከት ጋዜጠኛ በአግራሞት ከታዘበው ነገር ዋነኛው በህዝቡ ውስጥ ያየው የመሰረቅ ስሜት ነው:: ይህ የሙባረክ ስርአት የሰረቀባችው የህዝቡን ንብረት ብቻ ሳይሆን ከዚያም በላይ ውድ የሆነ ነገር ነው:: የአንድን የግብጽ ትውልድ እጣ ፈንታ ነው የሰረቀባችው ሆኖ የተሰማቸው::

በካይሮ ዩኒቨርሲቲ መምህር የሆኑ አንድ ምሁር በዚሁ የንጻነት አደባባይ ሲዘዋወሩ ውለው ማታ አሜሪካ ለሚኖር ወዳጃቸው ደውለው ያሉት ደግሞ "ናስር: ሳዳትና ሙባረክ ለ40 ዓመታት በዘረጉት የግፍ የአገዛዝ ስርአት በመንገፍገፍ እነጥፍጥፍ አድርገው ያራገፉብኝን የአገሬን የግብጽን ፍቅር: እነኝህ የጣህሪር አደባባይ ወጣቶች በ 15 ቀናት ውስጥ መለሱልኝ:: አሁን ከነሱ ጋር ሆኘ ብሞትም አይቆጨኝም" ነበር ያለው::

በመጀመሪያ በቱኒዚያ ከዚያም በግብጽ ያየናችው ህዝባዊ እንቅስቃሴዎች ብዙ ጉዶች አያሳየን ነው:: እጅግ በሚዘገንን የአፈና ስርዓት ውስጥ ተወልደው ያደጉ ወጣቶች እምቢ ለሙብቴ ብለው ያሳዩት የሚገርም ጀግንነት: ልጇ በእንቅስቃሴው የሞተባት እናት በልጇ መሰዋት የተሰማትን ክብር የገለጸችበትና ሌላው ወንድ ለጇ የሞተው ልጇን አላማ ከዳር እንዲያደርስ ስትማጸን በሰማንበት: አዲሱ የሙባረክ ምክትል ፕሬዜዳንት ሱሌይማን የግብጽ ህዝብ ገና ለዴሞክራሲ አለመብቃቱን ለአለም ህዝብ ያለማፈር ሲነግሩ: ከኛ በላይ ዴሞክራሲ ላሳር ነው ሲሉ የነበሩት የምእራብ መንግስታት በቶኒ ብሌር አማካኝነት ለግብጽ ህዝብ ከነጻነትና ከዴሞክራሲ ይልቅ መረጋጋት የበልጣል: የኛም ጥቅም የሚጠበቀው በሱ ነው ብለው ያለማፈር ሲናገሩ የሰማንበት ጊዜ ነው:: ይህ የብሌር ንግግር እጅጉን ያስከፋው እውቁ የዘመናችን ፈላስፋ እስላቮይ ጂጀክ ይህንን የምእራባውያን የታመቀ የዘረኛነት መገለጫ: "አረቦች ወይንም አፍሪካኖች ለዴሞክራሲ አልበቁም" የሚል የነጻነትን አለም አቀፋዊነት መርህ የሚጋፉ አሳፋሪ ትእይንት ብሎ ተሳልቆ: ግብጾች ለኛ ዴሞክራሲን ያስተማሩበት ክስተት ነው ብሎታል:: ወይዘሮ አና ጎሜዝ በግንቦት 97 ምርጫ ወቅት የህዝቡን የዴሞክራሲ ፍላጎት በምርጫው እለት ለሰአታት ተሰልፎ ዝናብና ሀሩር እየተፈራረቀበት በትእግስት: በሚገርም ዲሲፕሊንና በነቂስ ወጥቶ ሲመርጥ ተመልክተው ያሉትም ይህንንው ነበር::

ይህንን ተአምራዊ የነጻነት እንቅስቃሴና በወቅታዊ የሃገራችን ፖለቲካ ላይ ያለው እንድምታ ላይ ያለኝን አስተያየት ከማቅረቤ በፊት በዚህ ስብሰባ ላይ ተካፋይ እንድሆን ስለጋበዛችሁኝ ምስጋና ላስቀድም::

ንግግሬን ፈር ለማስያዝ እንደሚከተለው ከፋፍዬ አቀርባለሁ። በመጀመሪያ በሰሜን አፍሪቃና መካከለኛው ምሥራቅ እያየነው ባለው ክስተት ምንነት ላይ የራሴን ግንዛቤ አቀርባለሁ። ቀጥዬም ለዚህ ህዝባዊ መነሳሳት አስተዋጽኦ አድርገዋል ብዬ የማምናቸውን ጉዳዮች እያነሳሁ እኔ በገባኝ መንገድ ለመዳሰስ እሞክራለሁ። ከዚያ ቀጥሎ እስካሁን ካየነው የምንወስዳቸው ትምህርቶች ላይ አተኩራለሁ። በመጨረሻም ቱኒዚያ ውስጥ ተለኩሶ እየተቀጣጠለ ያለው የነፃነት ችቦ እኛ አገር እንዲደርስ ማድረግ ይኖርብናል ብዬ የማምናቸውን ነገሮች እነሳለሁ።

**ምንድነው እየሆነ ያለው?**

ሰሜን አፍሪካ እና መካከለኛው ምሥራቅ መሠረታዊ የሆነ የለውጥ ሂደት ውስጥ ናቸው። "አብዮት" የሚለውን ቃል መጠቀምም እንችላለን። ይህ አብዮት የአካባቢውን ጂኦ-ፓለቲካ ሙሉ በሙሉ ይለውጣል ተብሎ ይገመታል። አንዳንድ ሰዎች አብዮቱን የሰሜን አፍሪቃና የመካከለኛው ምሥራቅ ክስተት ብቻ አድርገው ሲወስዱት ይስተዋላል። ይህ ትክክል ስላለመሆኑ ተጨባጭ ማስረጃዎች አሉ። የቱኒዚያው ችቦ ነፀብራቅ በአውሮፓ በአልባኒያና ሰርቢያ፤ በሩቅ ምሥራቅ ደግሞ በኢራቅ ውስጥ በጉልህ ታይተዋል። በዩጋንዳና ናጄሪያም ውስጥ ብልጭታው ታይቷል። የያዝነው የአውሮፓውያን 2011 በሃይማኖትና በዲሞክራሲ ሽፋን ተንሰራፍተው ለተቀመጡ አምባገነኖች በሙሉ የሚመች ዓመት እንደማይሆን መልዕክቱ የተላለፈላቸው ይመስላል። ህዝብ ለአስር ዓመታት የሰማው ባዶ ስብከት የሰለቸው መሆኑ በግልጽ የተናገረበት አጋጣሚ ነው። ይህ ለውጥ የጽንፈኝነት አደጋ ባለባቸው አገሮች ውስጥ በሲቪል ሙብቶች ዙርያ ያጠነጠነ ንቅናቄ መሆኑ ይበልጥ አጓጊ አድርጎታል።

የሁኔታዎች ፍጥነት እጅግ አስገራሚ ነው። በቱኒዚያ ለሃያ ሶስት ዓመታት የተንሰራፋው አምባገነን በወር ውስጥ ወደቀ። በግብጽ ለ30 ዓመታት የተደላደለውና የኃያላን አገሮች ከፍተኛ ድጋፍ ያለው መንግሥት በ15 ቀናት ውስጥ ተነቀነቀ። በዮርዳኖስ፣ በየመንና አልጄሪያ ውስጥም የመንግሥታቱ ጥርሶች ተነቃነቁ። በአካባቢው ያሉት አምባገነኖች ካቢኔን መፐወዝ፤ ደመወዝ መጨመር፤ ዋጋ መቆጣጠር፤ "በሚቀጥለው ምርጫ አልወዳደርም" እያሉ ቃል በመግባት ማዕበሉን ለማቀዝቀዝ እየጣሩ ነው። ህዝባዊው ንቅናቄ ግን ይበልጥ ሥር እየሰደደና እየተሰራጨ እንጂ እየበረደ አይደለም።

የየመኑ አሊ አብደላ ሳልህ ገና የቱኒዚያውን ህዝባዊ አብዮት ሲያይ ለእሱም እንደማይቀርለት ተገንዝቦ በሚቀጥለው ምርጫ እንደማይሳተፍ፤ ሥልጣንን በማውረስ እንደማያምን በመግለጽ የወጣቱን አጀንዳ ለመንጠቅ ያደረገው እሽቅድድም አስገራሚ ነው። የሱዳኑ አልበሽርም "ብትፈልጉ በድጋይ ውገሩኝ እንጂ ከአገር አልወጣም" ሲል የአገሩን ወጣቶች "አንጀት ለማራራት" ሞከረ። የኢራቁ አልማለኪም ለሶስተኛ ጊዜ እንደማይወዳደር ቃል ገባ። ይህ ሁሉ ሆኖ ግን ቱኒዚያ ላይ የተለኮሰው ችቦ እየጎመራ ነው። ሌላው ቀርቶ ፍጹም የተዘጋች አገር በምትመስለው ሳዉዲ ዓረቢያ ውስጥ እንኳን ለመጀመሪያ ጊዜ የተቃውሞ ሰልፍ ተደረገ። በጎረቤታችን በጅቡቲም እየተንተከ ነው:: ይህ አብዮት እያዳረሰ ያለው በሃይማኖት ሰበብ የሲቪል ሙብቶች በሚረገጥባቸው አገሮች ውስጥም መሆኑ በአይነቱ ልዩ ያደርገዋል። ይህንን ሁሉ በአንድነት ስናስተውል ነው "ምንድነው እየሆነው ያለው?" የሚለው ጥያቄ መሠረታዊ መሆኑ የምንገነዘበው:: በዚህ ጉዳይ ላይ ወደፊት በርካታ ጥናቶች እንደሚደረጉ ጥርጥር የለውም። ወደፊት ብዙ ሊጨመሩባቸው የሚገቡ ነገሮች ቢኖርም እስካሁን በአየነው መነሻነት የሚከተሉት ድምዳሜዎች ላይ መድረስ ይቻላል ብዬ አምናለሁ።

1. ይህ ህዝባዊ አመጽ ያሳየን ነገር የነፃነትና የዲሞክራሲ ፍላጎት ዘርን፣ ባህልንና ሃይማኖትን ተሻጋሪ መሆኑን ነው። ነፃነትና ዲሞክራሲ ለምዕራባዊያን ባህልና ሃይማኖቶች የተመቹ፤ ለሌሎች ባህሎችና ሃይማኖቶች ጋር አብረው የማይሄዱ ተደርጎ ሲወሰድ ቆይቷል። "አረብና አፍሪካዊ ለሆዱ ሲል ቢረገጥ አይከፋውም" የሚል ሃሳብ ብዙ ጊዜ በስውር፤ አንዳንዴም በግልጽ ሲነገር ቆይቷል። የሰሞኑ የሰሜን አፍሪቃ ህዝባዊ አመጾች ይህንን አስተሳሰብ በማያንሰራራ ሁኔታ በታትኖታል። በተደጋጋሚ በፓሊሶች የሚደርስበት ውርደት ተሸክሞ ከሚኖር ራሱን ያቃጠለው ቱኒዚያዊው ወጣት መሃመድ ቦዛዚ በተግባር የነገረንም ይህንን ነው። እንደ አሜሪካዊ ወይም አውሮፓዊ ወጣት ሁሉ እሱም በራሱ ህይወት ላይ ራሱ የመወሰን መብት ያለው መሆኑን፤ ይህ መብት ከሚገፈፍ አለመኖሩ የሚመርጥ መሆኑን አሳይቶናል። ከካይሮው የጣህሪር አደባባይ ሰልፈኞች ጥያቄ በተለያየ መንገድ ይቅረብ እንጂ ማጠቃለያው "ባርነት በቃን! ውርደት በቃን!!" የሚል ነው።
2. ሰው ነፃነቱን ሲጎናፀፍ ለራሱ የሚሰጠው ክብር ምን ያህል ከፍ እንደሚል የሰሜን አፍሪካው ንቅናቄ አሳይቶናል። "እኔ ምን አቅም አለኝ" "የመጣውን መቀበል እንጂ ምን ማድረግ እችላለሁ" የሚል ሰው በታህሪር አደባባይ ህዝባዊ ተቃውሞ ውስጥ ማግኘት አይቻልም። እዚያ የተሰበሰ ሰው በሙሉ "የኔ ተሳትፎ ዋጋ አለው" ብሎ የሚያምን፤ በመሳተፉም ክብር የሚሰማው ነው። እንዲያው በዚህ ንቅናቄ ውስጥ መሳተፍ ራሱ የክብር መገለጫ ሆኗል። በዚህም ምክንያት ነው በርካታ ግብፃዊያን ከህዝባቸው ጋር ለመራብ እና ለመታገል ክብር ሲሉ ከአውሮፓና አሜሪካ የተመለሱት። በዚህም ምክንያት ነው ሰልፎቹ የተቃውሞ ሰልፍ ብቻ ሳይሆን የፍቅርና የአንድነት ማሳያ የሆኑት። ሰልፎቹ የደስታና የተስፋ ቦታዎች ሆነዋል። ሠርጋቸውን በታህሪር አደባባይ ያደረጉ ጥንዶችንም ሳይቀር አይተናል።
3. ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚመጣው የባለቤትነት ስሜት ነው። ወጣቶች የተቃዉሞ ሰልፎችን ለመጥራት እና ራሳቸውን በግንባር ቀደምትነት ለማሰለፍ ከማንም ፈቃድ ይሁን እርዳታ አልጠበቁም። ፓርቲዎች ወይም የታወቁ ሰዎች እንዲመሯቸው አልጠበቁም። ኃያላን መንግሥታት እንዲደግፏቸው አልተለማመጡም። እያንዳንዱ ሰው የራሱን ኃላፊነት ራሱ ወስዷል። ሰልፈኞች የግብጽ ባለቤቶች እኛ ነን ብለው በማመናቸው እርምጃዎቻቸው ሁሉ ኃላፊነት የተሞላው ነው። የግብጽ ሙዚየም ከዘረፋ የተከላከሉት ራሳቸው ሰልፈኖች ናቸው። ፓሊስ በጠፋ ጊዜ የፀጥታ አስከባሪዎች የወጡት ከራሱ ከሰልፈኛው ነው። መንገድ የሚጠርጉት እነኝሁ ታጋዮች ናቸው::

**በህዝባዊ አመፁ ዋዜማ አገራቱ የነበሩበት ሁኔታ**

ቱኒዝያ፣ ግብጽ፣ ዮርዳኖስ፣ የመንና አልጄሪያ ከአረብነት እና እስላም ሃይማኖት በተጨማሪ በርካታ የሚያመስሏቸው የጋራ ባህሪያት አሉዋቸው። አንዳንዶቹን ከዚህ በታች እዘረዝራለሁ።

1. **አምባገንነት:** በእነዚህ አገሮች ሥልጣን በአንድ ግለሰብ ወይም በአንድ አነስተኛ ቡድን መያዝ የተለመደባቸው ናቸው። ብዙዎች አምባገነኖች ከሃያ ዓመታት በላይ በመንግሥት ሥልጣን ላይ ቆይተዋል። እኚህ አምባገነኖች በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት መሪነት መቀየር ካስፈለጋቸው የሚመጠቀሙት ስልት ርስ በርሳቸው መተካካትን ነው። በዚህም ምክንያት ሥልጣን በአንድ ቤተሰብ የተያዘባቸው ነበሩ።
2. **የሴራ ምርጫዎች:** በእነዚህ አገሮች ሁሉ የሴራ ምርጫ ሲደረግባቸው የቆዩ ናቸው። የሴራ ምርጫ በስልጣን ላይ ያለው ኃይል እንደገና የሚመረጥበት አሊያም በሥልጣን ላይ ያለው አካል በሚፈልጋቸው ሰዎች የሚተካበት ድግስ ነው። እነዚህ አገሮች ተደጋጋሚ የሴራ ምርጫዎችን ማድረጋቸው "ዲሞክራሲ አስፍነናል" ብለው ለመመፃደቅ ረድቷቸዋል። ምዕራባዊያንም እውነተኛ ዲሞክራሲ ከምዕራቡ ዓለም ውጭ የማይሆን ነገር አድርገው ስለሚወስዱት "ሙከራ ማድረጋቸው" እራሱ እንደ ትልቅ ነገር እየቆጠሩት ሲያሞካሹዓቸው ቆይተዋል። (ክፍል 2 ሳምንት ይቀጥላል)

## የወያኔው አምባገነን አገዛዝ ኦብነግ ከፍተኛ ራስ ምታት ሆኖኛል ማለቱ ተጋለጠ

ዊኪሊክስ በቅርቡ ባጋለጠውና በቅርቡ ይፋ በሆነው የአሜሪካ ሚስጥራዊ ሪፖርት በኦጋዴን አካባቢ የሚደረገው የአማጽያን እንቅስቃሴ ከሚጠበቀው በላይ የወያኔውን አምባገነን አገዛዝ እንዳስጨነቀው ታወቀ። ዘረኛው የወያኔ አምባገነን አገዛዝ ከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ መግባቱን ያጋለጠው ዊኪሊክስ መሰረት ያደረገው በአዲስ አበባ የአሜሪካ አምባሳደር የሆኑት ዶናልድ ያማሞቶ በኖቬምበር 2007 በሚስጢር ያስተላለፉትን ዲፕሎማቲክ መልእክት መሰረት በማድረግ ነው ። እንደ ዊኪሊክስ መረጃ ዘረኛው አምባገነን አገዛዝ ከፍተኛ ጭንቀት ውስጥ የገባው "ህወሐት ከሁለት አስር አመታት በፊት የደርግን ጨካኝ ስርአትን ሲጥል የነበረበት ይዞታ ከዛሬው የኦብነግ ይዞታ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ስላገኘው ነው በማለት አምባሳደር ያማሞቶ መናገራቸውን ገልጹአል። " ያማሞቶ "ዘረኛው መለስና አቀንቃኙ የመከላከያ ሚኒስትር ኢታማዠር ሹም ጄኔራል ሳሞራ የኑስ ኦብነግን ሰፊ ድጋፍ ከማግኘቱ በፊት ማስወገዱ ወሳኝ ነው።" ብለው እንደሚያምኑ መጠቆማቸው ታውቁአል።

እንደ ዊኪሊክስ መረጃ አምባሳደሩ ይህንን ግምገማ በግላቸው ያቀረቡት ሳይሆን ከራሱ የኢትዮጵያ መንግስት የመነጨ መሆኑን መጠቆማቸውን፡- የወያኔው ቁንጮ መለስ፣ ከሳሞራና ከሌሎች የህወሐት/ኢህአዴግ አባላት ጋር ባደረጉት ውይይት "ኦብነግ ወደፊት የመንግስት ስጋት ከመሆኑ በፊት አሁኑኑ በወታደራዊ ክንድ መደቆሱ ወሳኝ ነው ብለው እንደሚያምኑ ግልጽ ሆኗል።" ብሉአል።

ዘረኛውና አምባገነኑ መለስ በኦብነግ ላይ ያደረትን ፍርሀት የሚገልጸው ግምገማ የተጠቀሰው ኦብነግ በአንድ የቻይና ነዳጅ ፈላጊ ቡድን ላይ ጥቃት ካደረሰና በአጸፋውም የመንግስት ጦር በጭካኔ የተሞላ የመልሶ ማጥቃት እርምጃ ከወሰደ ከጥቂት ወራት በኋላ ሲሆን የመልሶ ማጥቃቱ እርምጃ ከልክ ያለፈና ፍጹም በጭካኔ የተሞላ እንደነበር የስርአቱ ሁነኛ ወዳጅ የሆኑት አሜሪካዊው አምባሳደር ሳይቀሩ ማመናቸው ታውቁአል።

ይሄው የአሜሪካው ሚስጢራዊ መልእክት፤ ጦሩ ከልክ ያለፈ ሀይል መጠቀሙንና ንጹሀን የአካባቢውን ህዝብ በአማጺያኑና በመንግስት ኃይሎች መሀል አጣብቂኝ እንዲገባ እንዳደረገ በተለያዩ የሰበአዊ መብት ተሟጋቾች ቀርቦ የነበረውን ክስ ትክክለኝነት እንደተረጋገጠም ታውቁአል። ይሁን እንጂ ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ይህንን የሰበአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች ክስ አይኔን ግምባር ያድርገው በማለት በጽኑ ያስተባብለው እንደነበር ይታወሳል።

አምባሳደር ያማሞቶ በቻይና ነዳጅ ፈላጊዎች ላይ በኦብነግ የተወሰደው "በአስደንጋጭ ሁኔታ የተሳካ" ጥቃት ለምን በኢትዮጵያ መሪዎች ላይ ከፍተኛ ፍርሀት እንዳነገሰ ሲገልጹ፡- 'የመከላከያ ኃይሉ የነዳጅ ፍለጋ ጣቢያውን መከላከልም ሆነ በአጥቂዎቹ ላይ አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ ባለመቻሉ እፍረት የተከናነበበት በመሆኑ ነው።" ማለታቸውን ዊኪ ሊክስ አጋልጡአል። ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ኦብነግ በሽብርተኝነት እንዲመዘገብለት በአሜሪካና በጎረቤት የአፍሪካ ሀገራት ላይ ግፊት ቢያሳድርም እንኳን እስካሁን ከኬንያ በቀር የተቀበለ እንዳልተገኘ ይታወቃል፡፡

አምባገነኑና ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ዓለም አቀፍ የሆኑ የሰብአዊ መብት ጥበቃ ድርጂቶች የሚያቀርቡአቸውን ሪፖርቶች ሁሌም አይኑን በጨው እያጠበና አላየሁም አልሰማሁም እንደሚል የሚታወቅ ሲሆን ኡጋዴን ላይ የወሰደውን በጭካኔ የተሞላበትም ግድያ "የውጭ ሰርጎ ገቦችንና አክራሪዎችን" ለማስቆም ነው ማለቱን ቀደም ብለን መዘገባችን አይዘነጋም።

### ወያኔ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ይህ በንዲህ እንዳለ ሰሞኑን ሊቢያ ውስጥ ኮሎኔል ሙአመር ጋዳፊ በህዝባቸው የደረሰባቸውን ተቃውሞ ለመበተን ቅጥረኛ ገዳዮችን በገንዘብ አስመጥተው ሊቢያዊያንን ማስጨፍጨፋቸው የተዘገበ ሲሆን ጋዳፊ ቅጥረኛ ወታደሮችን ወደሃገራቸው ለማስገባት የተገደዱት የራሳቸውን ወታደሮች በመጠራጠራቸውና ትእዛዜን አይቀበሉም ከሚል ስጋት እንደሆን ታውቁአል ከዚሁ ጋር ተያይዞ አልጀዚራ የዜና አውታር በሊቢያዊያን ቁጥጥር ስር የዋሉ በርካታ ቅጥር ነፈሰ ገዳዮችን ከነፓስፖርታቸው ያሳየ ሲሆን ከዚህ ውስጥ የበርካታ ኢትዮጵያዊያን ፓስፖርቶች ታይተዋል ቀደም ብሎ ኢትዮጵያን ሪቪው በመባል የሚታወቀው የመረጃ ድረገጽ ባወጣው ጽሁፍ ከነኝህ የሊቢያ መንግስት ቅጥር ገዳይ ወታደሮች ውስጥ ኢትዮጵያዊያን እንደሚገኙበት መግለጹ ይታወሳል፡፡

### በጋምቤላ ክልል ከ4000 ሄክታር በላይ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በቅርቡ በፈረንሳዊያን ተዘጋጂቶ ለእይታ የቀረበ ጥናታዊ ፊልም ኢትዮጵያ ውስጥ በልማት ሽፋን ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ እያደረሰ ያለውን የሃገር ውድመት ያጋለጠ ሲሆን ይህ ፊልም በፈረንሳይና በስዊድን ሃገር የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች መተላለፉና በየሃገራቱ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንን እጂግ ማሳዘኑ አይዘነጋም፡፡

ወያኔ በሃይል ሥልጣን ከተቆጣጠረ ከ1983 ጀምሮ በትግራይ ክልል በየአመቱ ከፍተኛ የሆነ የዛፍ ተከላ ዘመቻ እያካሄደ እንደሚገኝ የታወቀ ሲሆን ባለቤትነት በማይሰማው የአገሪቱ ደቡብ፤ ደቡብ ምዕራብና ምዕራብ ክልሎች የሚገኘውን ጠቅጠቅ ያለ የተፈጥሮ ደን ያለምንም ርህራሄ እያስጨፈጨፈ እንደሆነ ግልጽ ሆኖአል፡፡ ድህረ ምርጫ 97 በባሌ ክልል የሚገኘውን በደን የተሸፈነ ብሄራዊ ፓርክ ሆን ብሎ በ ዕሳት እንዲጋይ እንዳደረገና የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች እሳቱን ለማጥፋት በዘመቻ እንዲሄዱ ጠይቀው እንደተከለከሉ ይታወሳል።

### በዋሺንግተን የወንድማማቾች ቀን በሚል ስያሜ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ቀጥሎም በሀገራችን ውስጥ እየታየ ያለው ሁኔታም ለሁላችን ግልፅ ነው። በአንድ በኩል በረሃብ የሚገረፍ፣ ለባዕድ ምፅዋትና ልመና ተጋልጦ ንሮውን መሸነፍ ያቃተው ህዝብ አለን። ህፃናት በቆሻሻ ቦታ የተጣለና የበሰበሰ አጥንት እየለቀሙ ከውሾች ጋር እየተሻሙ የሚበሉበት፣ በችግር ላይ ችግር የወደቀችና የደቀቀች ሀገር ነው የምናየው። በአንፃሩ በሙስና የናጠጡ ጥቂት ጉልበተኛ ቡድኖች ክብረ ልዕልናዋን ደፍረው፣ አንጡራ ሃብትዋን እየዘረፉ፣ ለም መሬትዋን እየሸነሸኑ ለባዕዳን በመቸብቸብ ህዝባችንን የበይ ተመልካች በማድረግ ረግጠውና አፍነው የሚገዙ አምባገነኖች የበቀሉባት ምድር ሆና ትገኛለች ካለ በኋላ እኛ በዲያስፓራ የምንገኘው ኢትዮጵያውያን ያለንን መለስተኛ የአመለካትና የእምነት ልዩነት ወደ ጎን ትተን በቅድሚያ ሀገርንንና ህዝብን ከመበታተንና ከጭቆና ማዳን ዋል እደር የማይባልበት ወቅቱ የሚጠይቀው ጉዳይ ነው ። ስለሆነም ጎሳ፣ ሀይማኖት፣ ፆታ፣ ህፃን፣ ሽማግሌ ሳይለይ እንደ አንድ ቤተሰብ ሁላችንም ተሰባስበን ለህዝባችን ያለንን የትግል አጋርነታችንን በጋራ የምንገልፅበትና ከጎኑ መሰለፋችንን በተግባር የምናሳይበት የትብብርና የቤተሰብ ቀን (people to people Solidarity day) በተቀናጀ መልኩ አዘጋጅተናል ብሎአል። በመሆኑም ይህ በልዩ ልዩ ፕሮግራሞች ታጅቦ የሚከናወን የወንድማማቾች ቀን ከወዳጅ ዘመዶቻችሁ ጋር አብራችሁ እንድትገኙልን የአክብሮት ጥሪያችንን እናቀርባለን። በማለት ጥሪውን አስተላልፎአል።

### በአዲስ አበባ ሳሪስ ሁለት ወጣቶች . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ዘረኛው የወያኔ አምባገነን አገዛዝ እየወሰደ ያለውን የእብዶች አይነት ስራ በሚመለከት አስተያየታቸውን እንዲሰጡን የጠየቅናቸው የፖለቲካ ተንታኝ በሰጡን አስተያየት አምባገነኖች መቆሚያ መቀመጫ የሚያሳጣቸው አጣብቂኝ ውስጥ እስኪገቡ ድረስ እስከ መጨረሻዋ ደቂቃ መፍጨርጨራቸው እንደማያስገርማቸው ገልጸዋል አስከትለውም እንዲህ አይነት አምባገነኖች የዘረኘነት ባህሪ ያላቸው ከሆኑ ደግሞ የሚሰሩት ሁሉ ለማመን የሚያስቸግር ጥፋት መሆኑ አይቀሬ ነው እናም የወያኔው አገዛዝ አባላት እንዲህ አይነት ርምጃዎችን መውሰዳቸው ህዝቡ በፍርሃት ተሸማቆ አጎንብሶ እንዲገዛላቸው ከሚያስቡት ከንቱ ቅዠት የሚመነጭ ተግባር ነው ያም ሆነ ይህ፣ ሊማሩ ቢችሉ ኖሮ ጠንካራና የተረጋጉ ናቸው በሚባሉት ግብጽና ቱኒዚያ የደረሰ ህዝባዊ አመጽ እዚህ መድረሱ አይቀሬነቱን ተረድተው በጊዜ ቢያመልጡ ይሻላቸው ነበር አለዚያ ግን እንዲህ አይነት ግፍና ጭካኔ የተሰራበት ህዝብ እነሱን ምን ሊያደርግ እንደሚችል መተንበይ ከባድ አይደለም በማለት ስተያየታቸውን አጠቃለዋል። ዶ|ር መራራ ጉዲና በአንድ ወቅት የሚበላውን ያጣ ህዝብ መሪዎቹን ይበላል ብለው አገዛዙን ማስጠንቀቃቸው ይታወቃል።

### አዲስ አበባ ከተማ ፊንፊኔ ተብላ እንድትጠራ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

አያይዘውም አዲስ አበባ ፊንፊኔ ተባለ አዲስ አበባ ሁለቱም የአገራችን ቋንቋ ውስጥ ያሉ ስያሜዎች ስለሆኑ ወያኔ አስገኘሁላችሁ ብሎ የሚያወራው ልማትዊ ዕድገት ያመጣቸው ወይም ዲሞክራሲ መግለጫ ይሆናሉ ተብሎ አንደማይታሰብ አይጠፋንም፣ ወያኔ ግን በተለመደ ብልጠትና ሴራው እያጠረበት ለመጣው የሥልጣን ዕድሜ ማራዘሚያ ህዝቡን ለመከፋፈል ያገለግለኛል ብሎ አስቦት ይሆናል ግን እንዳማያዋጣ ማን በነገረልኝ ካሉ ቦኋላ፣ ከቀደምቶቹ አምባገነን መሰሎቹ መማር እንኳ ቢያቅተው እንዴት ከሰሞኑ በሰሜን አፍሪካና በመካከለኛው ምስራቂ እየሆነ ካለው ህዝባዊ አመጽ መማር ይሳነዋል በማለት ይጠይቃሉ። ወያኔዎች ነፃ ሚዲያ የሚያስተላልፈውን ዜና እንዳንሰማ እኛ ብቻ የሚያፍኑ ነበር የሚመስለኝ አሁን አሁን ሳስበው አለም ላይ እየተከናወነ ያለውን እንዳይሰሙ ዕድሉን ለራሳቸውም ሳይነፍጉ የቀሩ አይመስለኝም ብለዋል።

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ወደስልጣን ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ ህዝብን በማከፋፈልና ርስ በርስ በማጋጨት የስልጣን ጊዜውን አራዝሞ እስካሁን እንደሚገኝ የሚታወቅ ሲሆን አሁን በተለይም ኢትዮጵያዊያን ጠላታቸው አንድና አንድ ይህም ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ መሆኑን በተገነዘቡበት ወቅት ከንቱና ባዶ የሆነ የመከፋፈል ሙከራ አገዛዙን የትም እንደማያደርሰው በርካታ የመገናኛ ብዙሃን በስፋት የሚዘግቡት ጉዳይ መሆኑ ይታወቃል።

### ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የአዲስ አበባ ቤት . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ከአነስተኛ ሽቀጣ ሽቀጥ ሽያጭ ገቢ በሚያገኙት ገንዘብ እንደሆነና ይህም ለኑሮአቸው ፈጽሞ ሊበቃቸው ባለመቻሉ ከሁለቱ ክፍል ቤት ሶስት ልጆቻቸውን ይዘው ወደ አንደኛው ክፍል ብቻ ለመኖር መገደዳቸውን ገልጸው በዚህ መንገድ ኑሮን ለመግፋት እያደረጉ ያለው ጥረት በደም መጣጩ ወያኔ አሁንም እየተደናቀፈ ነው በማለት በለቅሶ ተናግረዋል ቀጥለውም ቤታችንን ስንሰራም ሆነ ከዚያ በሁአላ ለኑሮአችን የሚበጅ አንዲትም ነገር ያላደረገ አገዛዝ ራሳችን ደም ተፍተን በሰራነው ቤት እንዴት ብሎ 40 በመቶ ታክሽ እንድንከፍለው እንደፈለገ አይገባኝም የያዝነው አመት ግፍ ሁሉ ሞልቶ የተረፈበት፣ ዘረኛው አገዛዝ ለህዝብ ያለውን ንቀት ከመቼውም በላይ አጉልቶ ያወጣበት ነው ብለዋል በመጨረሻም ወይዘሮዋ፣ ወያኔ በህዝብ ላይ እንዲህ ቀልዶና ግፍ ሰርቶ ረጂም ጊዜ እቆያለሁ ብሎ ማሰቡ ግን ከሞኝነት ያለፈ መጃጃል ነው ፣ የጊዜ ጉዳይ እንጂ ዋጋውን ማግኘቱ አይቀሬ ነው ብለዋል።

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በተለይም በ1997 ዓም በተካሄደው ምርጫ የአዲስ አበባ ከተማ ህዝብ አንድም መቀመጫ ወምበር እንዳያገኝ አድርጎ ጥላቻውን ከገለጻለት በሁአላ ተከታታይ የሆኑ የብቀላ ርምጃዎችን በህብረተሰቡ ላይ እየወሰደ እንደሆነ ይታወቃል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ ወይም በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org